# ለቤተሰቦች የድንገተኛ ጊዜ መረጃ መመሪያ

በዴንቨር የህዝብ ትምህርት ቤቶች(Denver Public Schools) ዉስጥ፣ የተማሪዎቻችን እና የሰራተኞቻችን ደህንነት ቀዳሚ ትኩረታችን ነዉ፡፡ የትምህርት ቤቱን ደህንነት ለማስጠበቅ የDPS የደህንነት ክፍል ከዴንቨር የፖሊስ ክፍል በተቀናጀ መልኩ ይሰራል፡፡ ወደ 200 የሚጠጉ ትምህርት ቤቶቻችን በከተማዉ የተሰራጩ ሲሆኑ፣ አንደ እኛ ከተማ አቀማመጥ መሰረት፤ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር የቅድሚያ ጥንቃቄ እርምጃዎችን በአብዛኛዉ ቀድመን እንወስዳለን፡፡

ማህበረሰቡን በእኛ ጥረት እና አላማዎች ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ቤተሰቦች ልጆቻቸዉን እና የአካባቢውን ሰራተኞች እንዲያግዙ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

## DPS ትምህርት ቤቶቻችን ለድንገተኛ አደጋ እንዲዘጋጁ ምን እያደረገ ነዉ?

- በየዓመቱ በትምህርት ቤት- የሚቀመጡ የዝግጁነት ቡድኖችን በድንገተኛ አደጋ ሂደቶች ላይ ማሰልጠን፡፡
- የድንገተኛ አደጋ እቅዶችን ትምህርት ቤቶች እንዲጨርሱ ማገዝ፡፡
- ከዴንቨር የፖሊስ ክፍል እና ከዴንቨር የአሳት ክፍል ጋር በመተባበር ተግባሮችን ማቀድለለ፡፡

## ቤተሰቦች ለማገዝ ምን ማድረግ ይችላሉ?

- ድንገተኛ አደጋ ወይም ዉጥረት በሚፈጠርበት ጊዜ ምን አንደሚፈጠር እንዲያዉቁ ለማድረግ ከልጆችዎ ጋር ስለትምህርት ቤት የአደጋ ጊዜ የምላሽሂደቶች መወያየት፡፡ ይህ መረጃ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚገኘዉ የሰራተኛ ቢሮ ፊት ለፊት ይገኛል፡፡
- የልጅዎ የአደጋ ጊዜ አድራሻ መረጃ የቅርብ ጊዜ መሆኑን ከትምህርት ቤቱ ጋር በተጨማሪም በወላጅ ፖርታሉ ላይ ያረጋግጡ (https://myportal.dpsk12.org) ፡፡ ተማሪች ከትምህርት ቤት ወጥተዉ ማንነቱ ላልተረጋገጠ ሰዉ አይሰከየአድራሻ መረጃዎ ትክክል ወይም የቅርብ ጊዜ ካልሆነ በድንገተኛ ጊዜ እርስዎን ለማግኘት አንችልም፡፡
- ልጅዎ መድሃኒት የሚወስድ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ በትንሹ ፣የሶስት ቀን አቅርቦት እንዳለዉ ያረጋግጡ፡፡

## ትምህርት ቤቶች ለድንገተኛ አደጋ ለመዘጋጀት ምን እያደረጉ ነዉ?

- ትምህርት ቤቶች ለድንገተኛ አደጋ ወይም ለዉጥረት የሚከተሉትን እርምጃዎች በመዉሰድ እንዲዘጋጁ ይጠበቅባቸዋል:
- የድንገተኛ አደጋ እቅድን በ DPS የደህንነት ክፍል ለድንገተኛ አደጋ አስተዳደር በመጀመሪ ሁለት የትምህርት ሳምንታት ማስገባት፡፡
- አመታዊ በትምህርት ቤቱ የሚገኝ የድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት ቡድኖች የምስክር ወረቀት ማግኘት፡፡ ሁሉም የድንገተኛ አደጋ ቡድን አባላቶች ፣ የድንገተኛ አደጋ ሂደቶችን ለመሸፈን፣ በደህንነት ክፍሉ የሚመራ ፣የኦንላየን ትምህርት እንዲከታተሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሁሉንም ተማሪዎች ያካተተ የድንገተኛ አደጋ ልምምዶች ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞቹ በተገቢዉ ደህንነት እና ጊዜ መመለስ መቻላቸዉን ለማረጋገጥ የደህንነት ክፍሉ እንዲታዘብ ይደረጋል፡፡ የእሳት አደጋ ልምምዶች በትምህርት አመቱ ሙሉ በየወሩ ይኖራሉ፡፡ የእንቅስቃሴ መቆም፣ መዘጋት እና የመጠለያ ልምምዶች በእያንዳንዱ ሴሚስተር የመጀመሪያ 30 ቀናት ይደረጋሉ፡፡
- በደህንነት ክፍሉ በአካል የሚደረጉ የድንገተኛ አደጋ ቡድን ስልጠናዎችን እንዲሁም የሰራተኛ ስልጠናዎችን ይሳተፉ፡፡

ዴንቨር የህዝብ ትምህርት ቤቶች የደህንነት መረጃ ክፍል | 1860 Lincoln St., Denver, CO 80203
720-423-3475 | Safety.dpsk12.org

# ስለ ትምህርት ቤቱ ድንገተኛ አደጋ ማወቅ የሚገባዎት ነገሮች:




## *የትምህርት ቤት መዘጋት ምንድነዉ?*

የደህንነት ጉዳይ ሲኖር ነገር ግን ትምህርት ቤቱን በቀጥታ የማያሰጋዉ አስጊ ከሆነ አንዲዘጋ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ፣ ፖሊስ አንድ መኪናን በትምህርት ቤቱ አካባቢ እያባረ ከሆነ ፣ እና የDPS ደህንነት ክፍል ትምህርት ቤቱ አንደቅድሚ ጥንቃቄ አንዲዘጋ ትእዛዝ ካስተላለፈ ሊሆን ይችላል፡፡ ሲዘጋ፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች በትምህርት ቤቱ ህንጻ ዉስጥ መቆየት አለባቸዉ፣ እና የትምህርት እንቅስቃሴዉ ተማሪዎች አና ሰራተኞች አንደ መደበኛዉ ጊዜ ደህንነታቸዉ በተጠበቀ ሁኔታ በትምህርት ቤት ዉስጥ እየተዘዋወሩ ይቀጥላል፡፡ መዘጋት ማለት ማንም ወደ ህንጻዉ አይገባም ወይም አይወጣም፣ በልዉዉጥ ጊዜ አስካልሆነ በስተቀር ተማሪዎች አና ሰራተኞች ይህንን ለዉጥ ላያስተዉሉት ይችላሉ፡፡




## *የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ መቆም ምንድነዉ?*

የትምህርት ቤቱን ደህንነት አደጋ ሊጥል የሚችል የደህንነት ነገር ሲኖር እንቅስቃሴ መቆም ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ፣ ፖሊስ አንድን ተጠርጣሪ በሚያሳድደበት ጊዜ ተጠርጣሪዉ በትምርት ቤቱ ንብረት ዉስጥ ከሆነ፡፡ የእንቅስቃሴ መቆም በተጨማሪ በትምህርት ቤት ዉስጥ አደጋ አለ ተብሎ በታሰበበት ጊዜም ሊደረግ ይችላል፡፡ እንቅስቃሴ ሲቆም ፣ የትምህርት ሂደቱ እና የክፍል አንቅስቃሴዎቹ ማቆም አለባቸዉ፣ እና ሁሉም ሰዉ ወደ ታች ሆኖ፣ በጸጥታ እና ከእይታ ዉጪ መሆን አለበት፡፡ የእንቅስቃሴ መቆሙ አስኪነሳ ድረስ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸዉ ዉስጥ በጸጥታ መቀመጥ አለባቸዉ፡፡

* በመዘጋት እና በእቅስቃሴ መቆም ጊዜ፣ የ DPS የደህንነት ክፍል ከድንገተኛ አደጋ ተከላካዮች ጋር በመቀናጀት ከትምህርት ቤት የሚለቀቁበትን ትክከለኛ ሰዓት ይወስናሉ፡፡




## *መጠለያ ማለት ምነድነዉ?*

መጠለያ ማለት ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ትምህርት ቤቱ ዉስጥ ባለ ደህና ቦታ ላይ ሲጠለሉ ነዉ፤ ይህም የመማሪያ ክፍል ወይም አዳራሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ለጤና አስቸጋሪ የሆነ ፣ ለምሳሌ አንደ አዉሎ ነፋስ ወይም የከፋ የአየር ማስጠንቀቂያ ሲኖር፣ እና ይህም በዉጪ በሚገኙ ኤጀንሲዎች እገዛ፣በደህንነት ክፍሉ፣ ማስለቀቁ ወይም ቅድሚ መልቀቁ፣ ተማሪዎችን አደጋ ላይ አንደሚጥል ሲወሰን ነዉ፡፡




## *መልቀቅ ምንድነዉ?*

መልቀቅ ማለት አንደ አሳት ባሉ ለጤና አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ፣ የሚደረስ ጉዳትን ወይም የአካል መጉደልን ለመከላከል ተማሪችን ከትምህርት ቤቱ ህንጻ ዉጪ አንዲወጡ ማድረግ ነዉ፡፡

## *የመገናኛ ቦታ ምንድነዉ?*

የመገናኛ ቦታ ማለት ለጤና አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ፣ በትምህርት ቤቱ ወስጥ ወይም ዉጪ ከሚደረስ ጉዳትን ወይም የአካል መጉደልን ለመከላከል ተማሪዎችን ከትምህርት ቤቱ አንዲለቁ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎች የሚገኙበት ቦታ ነዉ፡፡

## *በልጄ ትምህርት ቤት ዉስጥ መዘጋት እና የእንቅስቃሴ መቆም እየተካሄደ እንደሆነ እንዴት አዉቃለሁ?*

ወይም የማጣራት ሂደት አደጋ ላይ በማይጥል ሁኔታ መስጠት ነዉ፡፡ በተጨማሪም፣ የመረጃ የመስጠቱን እና በተማሪዎች ፣ ሰራተኞች እና ቤተሰቦች ላይ ተጨማሪ ዉጥረት ወይም ጭንቀት የመፍጠሩን ሁኔታ ማመጣጠን አስፈላጊ ነዉ፡፡

ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ ፣ በእኛ ፕሮቶኮል ላይ አንተቀመጠዉ የትመህርት ቤቱ መሪ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የሚያስፈልገዉን የመረጃ መጠን ይወስናል፡፡ መዘጋቱ በመዉጫ ሰዓት ወይም በመድረሻ ሰዓት ከሆነ ወይም ቤተሰቦች ላይ ተጽዕኖ ካለዉ ፣የትምህርት ቤቱን መሪ ቤተሰቦችን እንዲያናግር እናበረታታለን፡፡ የመረጃዉ መጠን በትምህርት ቤቱ ባሉ የቤተሰቦች ምርጫ ላይ ተመርኩዞ በትምህረት ቤቱ መሪ የሚወሰን ይሆናል፡፡

አንስቃሴ በሚቆምበት ጊዜ፣ የ DPS መረጃ ክፍል ከትምህርት ቤቱመሪ ጋር በመተባበር ለወላጅ የሚሰጠዉን ማስታወቂያ ያቀናብራል፡፡ የእቅስቃሴ መቆም የትምህርት ቤት አካባቢዉ ላይ መደበኛዉን እንቅስቃሴ በጣም ስለሚያዉከዉ፣ ቤተሰቦችን እንዲያዉቁት ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ አንዳንዴ፣ ቤተሰቦችን ለማሳወቅ DPS አዉቶማቲክ የስልክ መደወያ እና የኢሜይል መላኪያ ስርአቶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ከትምህርት ቤቱ ጋር በተጨማሪም በወላጅ ፖርታሉ ላይ የልጅዎ የአደጋ ጊዜ አድራሻ መረጃ የቅርብ ጊዜ መሆኑን አስፈላጊ ነዉ፡፡

## *በልጄ ትመህርት ቤት የመዘጋት/ የእንቅስቃሴ መቆም ተከስቶ ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?*

በልጅዎ ትምህርት ቤት አንቅስቃሴ መቆሙን/መዘጋቱ ከተነገርዎት ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ አይምጡ፡፡ ስለልጅዎ ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ሊቀበሉ የ ሚችሉበት ቦታ ላይ ሆነዉ ይቆዩ፡፡ ተማሪዎች ችግሩ እስካላለቀ ወይም ጉዳዩ የነበረበት ቦታ ለመልቀቅ ደህነነቱ እስካለተረጋገጠ ድረስ አይለቀቁም፡፡ ብዙ ጊዜ ባይከሰትም እንኳን፣ ተማሪዎች ከትምህርት ቤቱ ከተወደገዱ ልጅዎን ከመገናኛዉ ቦታ ለመዉሰድ ዝግጁ ይሁኑ፡፡

በወላጅ ፖርታል ዉስት የሚገኘዉን መረጃ የቅርብ ጊዜ በማድረግ(https://myportal.dpsk12.org)፣ አዉቶማቲክ የኢሜይል መልዕክቶችን እና አዉቶማቲክ የስልክ ጥሪዎችን ድንገተኛ አደጋ በሚደርስ ጊዜ ከትምህርት ቤቱ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ከወላጅ ፓርታሉ አካዉንትዎ የድንገተኛ አደጋ መረጃዎችን ለመቀበል መምረጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

### ድንገተኛ አደጋ ወይም ዉጥረት በሚከሰትበት መደረግ ያለባቸወ እና የሌለባቸዉ ነገሮች፡-

- የDPSን ድረ ገጽን ለቅርብ ጊዜ መረጃ ይጎብኙ (www.dpsk12.org)፡፡ በተጨማሪም፣ በዉጥረት ጊዜ የመጀመሪያ የዉይይት ሚዲያ የሆኑትን የ DPSን Twitter (@DPSNewsNow) እና Facebook (@DenverPublicSchools) ይጎብኙ፡፡
- የ DPS የቤተሰብ ስብሰባ ቀጥታ መስመር የሆነዉን 720-423-3054 እባክዎ ይደዉሉ፡፡
- ልጅዎ ከትምህርት ቤቱ ከተወገደ ስለ ዳግም ግኑኝነቱ የሚመለከተዉን መረጃ ማዳመጥ፡፡ ወደ መገናኛዉ ቦታ ትክክለኛ የመንግስት መታወቂያ ይዘዉ መምጣት ያስታዉሱ፡፡ ዳግም መገናኘቱ በአብዛኛዉ የማይከሰት እንደሆነ እባክዎ ያስተዉሉ፡፡
- እንዲመጡ ካልተጠየቁ በስተቀር ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት አይምጡ፡፡ ይህ የትራፊክ መጨናነንቅን ሊፈጥር እና የደንገተኛ አደጋ ሰራተኞችን ጥረት ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡
- ልጅዎን ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር አይደዉሉ፡፡ ከልክ ያለፉ ጥሪዎች የስልክ መስመሩን ሊያጨናንቁት እና በድንገተኛ አደጋ ንግግርን ሊያዉኩ ይችላለሉ፡፡

**የደህንነት ክፍሉ የዴንቨር የህዝብ ትምህርት ቤቶችን ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን ፣ ሌላ አካላቶችን እና ንብረቶችን ይጠብቃል፡፡ በዋና ማይክል ኤቶን የሚመራዉ፣ክፍል መርማሪዎችን፣ የታጠቁ ቁጥጥር አፊሰሮች፣ ተንቀሳቃሾች፣ የድንገተኛ አደጋ ፕሮፌሽናል፣ የደህንነት ቴክኒሺያኖች እና የካምፓስ የደህንነት አፊሰሮችን ጨምሮ ከ100 የሚበልጡ የቡድን አባላቶች የያዘ ነዉ፡፡ ክፍሉ በቀን 24 ሰዓታት፣ 7 ቀናት በሳምንት ዉስጥ, 365 ቀናት በዓመት ዉስጥ አገልግሎት ይሰጣል፡፡**

DENVER PUBLIC SCHOOLS
DEPARTMENT OF SAFETY